# ከዚህ በታች ላለው ጽሑፍ ርዕስ ይስጡ ቢባሉ ምን ይሉታል?

ከዚህ በታች ያለችውን ጽሑፍ በድረ-ገጻችን ላይ እንድናወጣ የላኩልን ሰው ርዕሱን "የዘሩት ዘር ሰብሉ ሲያምር" ብለውታል። አሲምባዎችና የኢሳት ሰዎች እሳትና ጭድ ከሆንን ሰንበትበት ብለናል። ለምን ቢባል ከአንድም ሁለት ጊዜ ኢትዮጵያን ለዚህ ያበቃትና ለብዙ ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ካለፍርድ መታረድ ተጠያቂውን፤ ከተደበቀበት ጉሮኖ ተጎትቶ ለፍርድ ሊቀርብ የሚገባውን ፋሺሽት በማናለብኝነት መድረክ መስጠታቸው ነው። ከዚያ በኋላማ ኢሳት የኢትዮጵያ ህዝብ ጆሮ ሲባልለትና ሲደለቅለት የነበረው የብዙሃን መገናኛ የግንቦት ሰባትና የሻቢያ የፕሮፓጋንዳ በሬ ወለደ ማደናቆሪያ ጣቢያ መሆኑን ለተከታተለው ሁሉ ግልጽ እየሆነ የመጣበት ጊዜ ሲሆን፣ እኛን የዚህ ጽሑፍ መልዕክቱ ፕሮፌሰሩ የግንቦት ሰባት ጽንሰ ሃሳብ ጥንሳሽና ባለቤት ነበሩ ማለቱ ነው? ወይንስ ምን ማለቱ ነው? ለማንኛውም የኢትዮጵያን ፖለቲካ የሚያምሱትን ለምትከታተሉ እስኪ ይህችን መጣጥፍ ያንብቡና ርዕስ ይስጡልን። በኛ በኩል እንኳን ብዙ ማለት አንፈልግም። ስሜታችንን ከዚህ በታች ያለው ስዕል ስለሚገልጸው በዚሁ እንተወዉ።



እስኪ እርስዎ አንባቢ ርዕስ ይስጡልን።

# የዘሩት ዘር ሰብሉ ሲያምር፣



የሰብአዊ መብት ተካራካሪው ፣ደራሲው፣መምህር መስፍን ወልደማሪያም፣ የኢትዮጵያን ሳታላይት ቴሌቪዥን ጣቢያ (ኢሳትን) ሲጎበኙ ሳይ የተሰማኝ ደስታ ወሰን የለውም፤ የኢሳት ባልደረባዎች ፣ በዓለም ዙሪያ ተበትነን የምንኖር ኢትዮጵያዊያን ውጤት ቢሆንም፣ እኛም የፕሮፌሰር መስፍን ወልደማሪያም ውጤት ነን እንላለን፤ ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማሪያም የሀገራች ሕዝብ ትክክለኛውን መረጃ እንዲያገኝ ህይወታቸውን በሙሉ መጣራቸውን ሥራቸው ይናገራል። ዛሬ ኢሳትን የመሰለ ለሕዝብ ትክክለኛ መረጃ የሚያቀርብን ተቋም በማየታቸው ለክ የዘሩት ዘር ሰብል እንዳመራላቸው ያህል ነው። በዚህ አጋጣሚ በውጭ የምንኖር ኢትዮጵያውያን ባቋቋምነው ተቋም ኮርተናል፣ ይበልጥ እንድንሰራ ፣የፕሮፌሰርን መስፍን ወልደማሪያምን ተመስሌት የሆነውን ለቆሙለት ዓለማ ሳይወላውሉ መፅናትን በኢሳት ማሳየት አለብን።

ታደለ መኩሪያ ከቫንኮቨር
tadele@shaw.ca